# የንባብ ትምህርት ሲሰጥ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጣቸው ትኩረት ፍተሻ

መዓዛ ደጄኔ [1] ጌታቸው እንዳላማው[2]

## አጽርሆተ ጥናት

*‹‹የንባብ ትምህርት ሲሰጥ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጣቸው ትኩረት ፍተሻ›› በሚል ርዕስ የተሰራው ጥናት ዋና ዓላማ በንባብ ትምህርት ጊዜ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጣቸውን ትኩረት መፈተሽ ነው፡፡ መሰረታዊ ጥያቄዎቹም ለየትኞቹ የንዑሳን የንባብ ክሂሎች የበለጠ ትኩረት ይሰጣል? የጥናቱ ተተኳሪዎች መምህራንስ ስለ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ያላቸው ግንዛቤ ምን ይመስላል? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ይሞክራል፡፡ በመሆኑም እነዚህን የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ በጥቅም ላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች በቪዲዮ ቀረጻ የታገዘ ምልከታ፣ የመምህራንና የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ፣ እንዲሁም ቃለመጠይቅ ናቸው፡፡ንዑሳን የንባብ ክሂሎች በተጠኚ መምህራኑ የተሰጣቸው ትኩረት አነስተኛ ነበር፡፡ተጠኚ መምህራኑ ንዑሳን የንባብ ክሂሎችን የሚያስተምሩት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ባሉት ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ላይ ብቻ የተወሰነ ሆኖ ታይቷል፡፡ በንባብ ትምህርት የአቀራረብ ደረጃዎች ቅድመ ንባብ ደረጃ በተሻለ ሁኔታ የተተገበረ ሲሆን፣በጊዜ ንባብ ደረጃ ያሉ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች በአብዛኛው ተዘንግተው ታይተዋል፡፡ ለምሳሌ የዝምታ ንባብ፣የአሰሳ ንባብ፣ የገረፍታ ንባብ ባለመተግበራቸው የንባብ ትምህርቱ ይሰጥ የነበረው በተማሪዎች ወይም በመምህራን እየተነበበ ነበር፡፡ በድህረ ንባብ ደረጃ መዳበር ካለባቸው ንዑሳን የንባብ ክሂሎች የምንባቡን አጠቃላይ ሃሳብ መረዳት ንዑስ ክሂል የንባብ ትምህርት ከሌሎች ጋር ማጣመር ንዑስ ክሂል ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸው ሲሆን የቀረበውን ምንባብ መገምገም ደግሞ አነስተኛ ትኩረት እንደተሰጠው ጥናቱ አመላክቷል፡፡ መምህራኑም ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በመጨረሻም የታዩትን ድክመቶች ለማሻሻል ሊያግዙ ይችላሉ የተባሉ የመፍትሔ ሐሳቦች በመጠቆም ጥናቱ ተቋጭቷል፡፡*

**ቁልፍ ቃላት፤ የንባብ ትምህርት፣ ንኡሳን ኪሂሎች፣መቀበያ ከሂል፣የንባብ ደረጃ፣ ምንባብ**

[1] PhD in Applied Linguistics Ethiopian Languages Teaching, Salale University

[2] PhD in Applied Linguistics Ethiopian Languages Teaching, Addis Ababa University

## 1.መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች አንዱ ንባብ ነው፡፡ ንባብ የመቀበያ ክሂል(Reseptive Skill) በመባል ይታወቃል፡፡ ስለ ንባብ በርካታ ጸሀፍት የራሳቸውን ብያኔ ሰጥተዋል፤ ከነዚህ መካከል Davies(1995፣1)ሲገልጹ ንባብ ግላዊና የአእምሮ ተግባር ነው ሲሉ May(1990፣10) በበኩላቸው ንባብ ከተጻፉ ምልክቶች ውስጥ ፍቺን ማግኘት ወይም በጽሁፍ የተቀረበን መልዕክት የመገንዘብ ሂደት ነው በማለት ገልጸውታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ Grellet(1981፣3) Nuttal(1982፣2) Simth(1985፣102)Wallace(1992፣4) ሲገልጹ ንባብ አንድ ጽሁፍ በውስጡ የያየዘውን መረጃ በበቂ ሁኔታ መገንዘብ ነው፡፡ ይህም ከቀረበው አነስተኛ ጽሁፍ ግንኙነት መፍጠር ነው፡፡ ይህን ለመፍጠር ደግሞ የአንባቢውን የመገንዘብ ችሎታ ይጠይቃል፡፡ ይህም የሚያሳየው ንባብ ግላዊና አእምሮአዊ ተግባር መሆኑን ነው፡፡ በተጨማሪም አለም(1995) Alderson et.al (1984፣1)ን ዋቢ አድርገው እንደገለጹት "የንባብን ምንነት በቀላሉ መመለስ የዋህነት ነው፤ንባብ በራሱ ውስብስብ የሆነ አእምሮታዊ ሂደት ነው"፡፡

ከላይ የተገለጸው የንባብ ምንነት በተመለከተ ምሁራን የሰነዘሩትን ሀሳብ ሲሆን፣ በሌላ በኩል የንባብ ትምህርትን በክፍል ውስጥ በማስተማር ረገድ ያለውን ችግር ለመፍታት Celce-Murcia (1991፣202) የራሳቸውን ንድፈ ሀሳባዊ ትንተና ሰጥተዋል፡፡ የንባብ ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ በዘመናዊ የማስተማር ዘዴ ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም ነው ለንባብ ትምህርት ለውጥ የተሻሻሉ የማስተማር ዘዴዎች እጅጉን አስፈላጊ ናቸው በማለት Atkins et.al. (1996፣55) አበክረው የገለጹት፡፡

በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተማሪዎች የንባብን ትምህርት በሚማሩበት ጊዜ ተግባራዊ የሚያደርጓቸው ንዑሳን የንባብ ክሂሎች አሉ፡፡ እነዚህ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች በጣም ጠቃሚና ተማሪዎች ችግር ፈቺዎች እንዲሆኑ የሚያግዙ ናቸው፡፡ በንባብ ትምህርት ጊዜ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጠው ትኩረት የንባብ ትምህርት የበለጠ ውጤታማ እንዲሆን እገዛ ይሰጣል (Hosenfel 1979 እና Rivers 1987)፡፡ በንባብ ትምህርት ሂደት የመምህሩ ተግባር ተማሪዎች ለንባብ ማስተማሪያ የተዘጋጁ ጽሁፎችን አንብበው የተለያዩ ክሂሎችን እንዲያዳብሩ መርዳት ነው፡፡

ስለ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ጸሀፍት የተለያየ አመለካከት አላቸው፡፡ አንዳንዶቹ እስከ ሰላሳ ስድስት ይደርሳሉ ሲሉ፣ አንዳንዶች ምሁራን ለምሳሌ Grellet (1981፣4-5) እና Munby(1978፣256) ደግሞ ወደ አስራ ዘጠኝ ያደርሷቸዋል፡፡ ከድረ ገጽ(2007) http://www.sed.org/pubs/reading/ የተገኘው መረጃ ደግሞ አስራ ሁለት እንደሚደርሱ ይጠቁማል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ Greenall and Swan(1986፣2) ንባብን በተሳካ መልኩ ለማካሄድ የሚያስችሉ አስራ ሁለት ያህል ንዑሳን ክሂሎችን በመዘርዘር አስፍረዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የንባብ ትምህርት ሲሰጥ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጠው ትኩረት ምን ይመስላል? የሚለውን በዝርዝር ማየት የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ነው፡፡ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የንባብ ትምህርት የዳበረ እንዲሆን ተማሪዎች ንባብን ከህይወታቸው ጋር በማያያዝ እንዲጠቀሙበት ለማስቻል የመምህራን ድርሻ ከፍተኛ መሆን አለበት፡፡ በዚህ ረገድ ለተማሪዎች የሚመረጡ የንባብ ማስተማሪያ ጽሁፎች ተማሪዎችን ለንባብ የሚያነሳሱ መሆን ይገባቸዋል፡፡ ይህም የንባብ ትምህርቱን የተሳካ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ መምህራንም ራሳቸውን ከዘመናዊ የንባብ ትምህርት አቀራረቦች ጋር በማዋሀድ በዘርፉ የሚፈለገውን ለውጥ ማምጣት ይጠበቅባቸዋል (Atkins et.al.1996፣56) ፡፡

ከዚህ በመነሳት በንባብ ትምህርት ዙሪያ መምህራን "ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጧቸው ትኩረት" በሚል ርዕስ ዙሪያ ጥናት ለማድረግ መነሻ የሆነኝ በአንዳንድ የጥናት ጽሁፎች ውስጥ (ሂሩት(1996)፣ማርታ(1992)፣እስጢፋኖስ(1993)፣ማስተዋል(1989)) የተሰጡት ጥቆማዎች፣ ለሴሚናር ኮርስ ማሟያ የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አሰጣጥ ላይ ያስተዋልኩት አቀራረብ ችግር ነው፡፡ ከችግሮቹ መካከል የንባብ ትምህርት በተለምዷዊ በ□ክታ ንባብ ሁኔታ የሚሰጥ መሆኑ፣ በንባብ ትምህርት ጊዜ የንባብ አይነቶችን እንደ አስፈላጊነታቸው አለመጠቀማቸው፣ የተማሪዎች ተሳትፎ ውስን መሆኑ፣ የተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታና ፍላጎት ዝቅተኛ መሆን የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡

### 1.2. የጥናቱ ዋና ዓላማ

በከፍተኛ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የንባብ ክሂል ትምህርት በሚያስተምሩበት ወቅት ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጡት ትኩረት ምን ይመስላል? ያላቸው ግንዛቤስ ምን ያህል ነው?የሚሉትን ጉዳዮች መመርመር የዚህ ጥናት ዓብይ ዓላማ ነው፡፡

በዚህ ጥናት ትኩረት ተሰጥቶ ፍተሻ የሚደረገው ንዑሳን የንባብ ክሂሎችን በተመለከተ ነው፡፡ ይህ ጥናት በሂደት ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል ተብሎ ይታሰባል፡፡

1. በንባብ ትምህርት ወቅት ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጣቸው ትኩረት ምን ያህል ነው?

2. በንባብ ትምህርት ወቅት ለየትኞቹ ንዑሳን ክሂሎች የበለጠ ትኩረት ይሰጣል?

3. መምህራንስ ስለ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ያላቸው ግንዛቤ ምን ይመስላል?

**1.3.የጥናቱ ጠቀሜታ**

በቋንቋ ትምህርት ጊዜ ትምህርት መሰረት የሚያደርገው በተዘጋጀው የማስተማሪያ መጽሐፍ ላይ ነው፡፡ መጽሐፉ ላይ የቀረቡ የንባብ ትምህርት ይዘቶች ደግሞ የሚተገበሩት በመምህሩ ነው፡፡ መምህሩ የቀረቡለትን የትምህርት ይዘቶች የሚያቀርብበት የማስተማር ዘዴ የታሰበውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ያስችለዋል፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

1. በቋንቋ ትምህርት በመማር ማስተማሩ ሂደት ወሳኝ ሚና ያላቸው የመማሪያ መጻሕፍት ንባብን ለማስተማር ምን ሁኔታን ይዘው መገኘት እንዳለባቸው ይህ ጥናት ለመማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች የማስተማሪያ መጻሕፍትን ለማሻሻልም ሆነ ለማዘጋጀት የበኩሉን መረጃ ይሰጣል፡፡
2. የመምህራን ስልጠና ለሚሰጡ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ተቋማት ሀሳብ ይሰጣል፡፡
3. አማርኛ ቋንቋ መምህራን የንባብ ክሂል ትምህርት ሲሰጡ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጡት ትኩረት ምን መሆን እንዳለበት ጥቆማ ይሰጣል፡፡
4. ይህ ጥናት ወደፊት በንባብ ዙሪያ ጥናት ለማካሄድ ለሚነሳሱ ጥናት አቅራቢዎች መነሻ ሊሆኑ የሚችሉ ሀሳቦችን በመጠቆም ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

**1.4. የጥናቱ ወሰን**

ጥናቱ ትኩረት የሚያደርገው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጡት ትኩረት ምን ይመስላል የሚለውን መፈተሽ ብቻ ይሆናል፡፡ ጥናቱ መምህራን ለንዑሳን የንባብ

ክሂሎች የሚሰጡትን ትኩረት ከመፈተሽ ሌላ የማስተማሪያ መሣሪያዎች፣የተማሪዎች የንባብ ችሎታ፣የተማሪዎች ንባብ የማንበብ የተነሳሽነትና የመሳሰሉት ላይ ፍተሻ አያደርግም፡፡

**2.ክለሳ ድርሳን**

**2.1.የንባብ ንዑሳን ክሂሎች**

ንባብ ሲባል በጽሁፍ የቀረበን ሀሳብ መረዳት ነው፡፡ ይህንንም ለማከናወን መዳበር የሚገባቸው ንዑሳን የንባብ ክሂሎች አሉ፡፡ እነዚህ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች እርስ በርስ በመዋሃድ አንብቦ የመረዳትን ሂደት ያጠናክራሉ፡፡ በንባብ ትምህርት ዙሪያ ጥናት ካደረጉት ምሁራን መካከል ለምሳሌ Alderson and Urqunent eds.(1984) በመጽሐፋቸው መግቢያ ላይ እንደገለጹት የንባብ ችሎታ መዳበር የንባብ ንዑሳን ክሂሎች መዳበር ውጤት ነው፡፡

Geenalls and Swam (1986፣3-4)ደግሞ ስለዚህ ርዕሰ ጉዳይ እንደገለጹት ተማሪዎች ሲያነቡ የሚያዳብሯቸው ንዑሳን የንባብ ክሂሎች አሉ፡፡ እነዚህም ያልተመለዱ ቃላት ፍቺ ከምንባቡ አውድ መረዳት መቻል፣ጽሁፍን አደረጃጀት መረዳት፣ አጠቃላይ ግንዛቤን ማግኘት መቻል፣የመገመት ችሎታ የጽሐፉን መልዕክት መረዳት እና ጽሐፉን መገምገም የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ንዑሳን የንባብ ክሂሎችን ብዛት በተመለከተ ምሁራን የተለያየ ዝርዝር ሲያውጡ ይስተዋላል፡፡ አንዳንዶቹ ምሁራን ለምሳሌ Alderson and Urqunent eds.(1984)Lunzer and Graner(1979፣42) ዋቢ አድርገው አስራ ሁለት መሆናቸውን ይጠቁማል እነሱም፣ የመገመት ችሎታ፣ ዋናውን ሀሳብ ማግኘት፣ የቀደመ እውቀትን መጠቀም፣ዋናው ነጥብ ላይ በማተኮር ማንበብ፣ በርጋታ ማንበብ፣ የቃላትን ፍቺ ከአውዱ ለመረዳት መሞከር፣ አንብቦ ለመረዳት የቃላትን አገባብ ለመረዳት መሞከር፣ንባብን በፍጥነት ማከናወን፣በንባብ ጊዜ ለግንዛቤ ጊዜ መውሰድ፣ያነበቡትን ጽሐፍ በአጭሩ ማስፈር፣የንባቡ ዓላማ መለየት፣ የጽሑፉን አይነት መለየት ናቸው፡፡

ከዚህ ሌላ እንደ Grellet(1981፣4-5) ገለጻ ንባብ በርካታ ንዑሳን የንባብ ክሂሎችን በውስጡ ይዟል ዋና ዋናዎቹ ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፤ የቋንቋውን የአጻጻፍ ስርዓት መለየት፣የቃላትን ፍች ከቀረበው አውድ ለመረዳት መሞከር፣በግልጽ የተነገሩ መረጃዎችን መረዳት፣በተዘዋዋሪ የተነገሩ መረጃዎችን መረዳት፣የቀረበውን ጽንሰ ሀሳብ መረዳት፣የዐረፍተ ነገሮችን ተግባርና አገላለጻቸውን

መረዳት፣በዐረፍተ ነገሮች መካከል ያለውን ግንኙነት መረዳት፣የጽሁፉን አካል በሰዋስው አያያ□ ች መካከል ያለውን ግንኙነት መረዳት፣የጽሁፉን ጠቃሚ ነጥቦች በአጭሩ መናገር፣መጻፍ፣ጽሁፉን በሌላ አመለካከት ለመተርጎም መሞከር፣በዲስኩር ውስጥ ያሉትን አመልካቾች መለየት ዋናና ዝርዝር ነጥቦችን መለየት የጽሁፉን ዋና ነጥብ በአጭሩ መግለጽ ከጽሁፉ ጠቃሚ ነጥቦችን ለይቶ ማውጣት፣የአሰሳ ንባብ፣የገረፍታ ንባብ፣ የቀረበውን መረጃ በስዕላዊ ሁኔታ ለመግለጽ መሞከር ናቸው፡፡ እነዚህ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ዝርዝር የተወሰዱት `Munbys Communicative Syllabus Design` ከሚሰኘው መጽሐፍ ነው፡፡

ከላይ በተለያዩ ምሁራን የተገለጹት ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ቁጥር የተለያዩ ስለመሆናቸው የተለያዩ ምክንያቶች አሉ፡፡ ከምክንያቶች መካከል የሚጠቀሱት አንዳንዶቹ ምሁራን (Alderson and Urqunent eds.(1984)Lunzer and Graner(1979፣42)) ንዑሳን የንባብ ክሂሎች አንዳቸው በአንዳቸው ስር ሊጠቃለሉ ይችላሉ የሚል አስተያየት አላቸው፤አንዳንዶቹ ደግሞ ንዑሳን ክሂሎች ተብለው በመነጣጠል መጠቀስ የሌለባቸው ነገር ግን የንባብ ሂደት ናቸው የሚል የመከራከሪያ ነጥብም ያነሳሉ፡፡

በተጨማሪም ንዑሳን የንባብ ክሂሎች እንደ አንባቢው የችሎታ ደረጃ ሊለያዩ ይችላሉ የሚል ነጥብም አለ፡፡ይህን ሀሳብ ከሚያነሱት ምሁራን መካከል ለምሳሌ Alderson and Urqunent eds.(1984)ዋቢ አድርገው እንደገለጹት የተለያዩ የጥያቄ አይነቶች የሚመለሱት የተለያየ የንባብ ንዑስ ክሂል ችሎታ ነው፡፡ ለዚህም ምሳሌ ሊጠቀሱ የቃላትን ፍቺ የመለየት ንዑስ ክሂልና በተዘዋዋሪ የቀረበ ጽሁፍን መልዕክት መረዳት አንድ አይነት ችሎታን የሚለካ አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ቁጥር የተለያየ መሆን የተለያዩ ምሁራን ከሚነሱበት የመገምገም ደረጃ ሊመነጭም የሚችል መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

## 3.የጥናቱ ዘዴ

### 3.1. የናሙና አመራረጥ ዘዴ

#### 3.1.1.የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ የተካሄደው በአዲስ አበባ ክልላዊ ከተማ መስተዳድር ነው፡፡ የጥናቱ ክልል የተመረጠው አመቺ ናሙና አመራረጥን በመጠቀም ነው፡፡ አዲስ አበባ ከተማ ክልላዊ መስተዳደር የተመረጠበት ምክንያት አጥኚዋ ካላት የጊዜና የገንዘብ መጠን ለጥናቱ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ወካይ ናሙና በዓይነትም ለመጠንም ሊገኝ ይችላል የሚል እምነት ስላላት ነው፡፡

በዚህ ጥናት የተካተቱት በአዲስ አበባ መስተዳድር ከሚገኙ ሀያ አንድ ሁለተኛ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ሶስት ብቻ ናቸው፡፡ በዚህ መሠረት ቦሌ፣ጥቁር አንበሳ እና ድላችን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በዕጣ የናሙና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ ይህም የተደረገው ለትምህርት ቤቶቹ እኩል ዕድል ይሰጣል ተብሎ ስለታሰበ ነው፡፡

### 3.1.2.የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

በዚህ ጥናት የዘጠነኛ ክፍል ደረጃ በአመቺ የናሙና አመራረጥ ስልት ተመርጧል፡፡ በዚህ ምክንያት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ለዚህ ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ በታሰበበት ጊዜ በትምህርት ላይ ስለሚገኙ በቂ ጊዜ እንዲኖራት ስለሚያስችላት ነው፡፡ በተጨማሪም የ9ኛ ክፍል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚጀመርበት በመሆኑ ችግሩን ለመለወጥ ጥረት በማድረግ ለቀጣዮቹ የክፍል ደረጃዎች አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡

### 3.1.3.የመምህራን ተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

**የተጠኝ መምህራን ናሙና አመራረጥ**

በሶስቱ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከሚያስተምሩ 13 የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በትምህርት ደረጃቸው በማስተማር ልምዳቸው ተቀራራቢነት ያላቸው ሁለት ሁለት መምህራን ከሶስቱ ትምህርት ቤቶች በአጠቃላይ 6 መምህራን ተመርጠዋል፡፡ ይህም የተከናወነው መረጃው ከየትምህርት ቤቶች የትምህርት አስተዳደር ቢሮዎች ከተወሰደ በኋላ ነው፡፡

**የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ**

ከሶስቱ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ትምህርት ቤቶች ውስጥ በመማር ላይ ካሉት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል ተጠኝ መምህራኑ በሚያስተምሩባቸው በእያንዳንዱ መማሪያ ክፍል ውስጥ 65-70 ተማሪዎች በአማካይ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም መካከል ከእያንዳንዱ ምልከታ ከተደረገበት ክፍል ወካይ ተማሪዎችን ለመምረጥ ከክፍሉ ተማሪዎች አንድ ሶስተኛው ያህል ተወስደዋል፡፡ የተማሪዎቹ መረጣም የተካሄደው በአንደኛ ወሰነ ትምህርት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤታቸው ከፍተኛ አማካይ ዝቅተኛ ውጤት ያላቸው ተማሪዎች ከተለዩ በኋላ ከየምድቡ(ከፍተኛ፣አማካይ፣ዝቅተኛ ውጤት)በአማካይ ሶስት ተማሪዎችን በመወሰድ ነው፡፡ የተፈለገውን ያህል ለመውሰድ የዕጣ ናሙና ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ በተለያየ የችሎታ ደረጃ ላይ የሚገኙ ተማሪዎችን በጽሑፍ ለማካተት ሲባል ነው፡፡በዚሁ መሠረት የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉ 70 ሴት ተማሪዎችና 62 ወንድ ተማሪዎች በአጠቃላይ 132 ተማሪዎች ናቸው፡፡

### 3.2.. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

የክፍል ውስጥ ምልከታ የዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው፡፡ የክፍል ውስጥ ምልከታ የተካሄደው ውስን የምልከታ ስልት በመጠቀም ነው፡፡ ውስን ምልከታ የሚባለው በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚደረገው የመማር ማስተማር ሂደት ላይ ከሚታዩት ክንውኖች ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች ቀደም ብሎ የመከታተያ ቅጽ አዘጋጅቶ መከናወኑን ወይም አለመከናወኑን በማየት መመዝገብ ነው፡፡

ይህንንም የምልከታ መከታተያ ቅጽ በመጠቀም በናሙናነት በተመረጡት 6 የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ክንዋኔ ለሶስት ጊዜ ያህል የምልከታ ግምገማ ተካሄዷል፡፡ ምልከታውም የተካሄደው በአጥኝዋና በሶስት ረዳት ተመልካቾች አማካኝነት ነው፡፡ ረዳት ተመልካቾች ሶስት የሆኑበት ምክንያት ሁሉንም አንድ ረዳት ተመልካች መከታተል ስለማይችል ነው፡፡ በምልከታውም የተለያዩ ሰዎችን አሰራር ለማካተት ሲባል የተለያየ የጊዜ ሰሌዳ በማውጣት በአመቺ ሁኔታ በመመደብ እየተፈራረቁ ምልከታው ተካሂዷል፡፡ ረዳት ተመልካቾች በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በስነ ትምህርት ኮሌጅ የአራተኛ ዓመት የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች ናቸው፡፡ ከምልከታው በፊትም ከአጥኚዋ ጋር በቂ የጋራ ውይይት ተደርጎ ስለ አሰራሩ በቂ መረጃ ተሰጥቷዋል፡፡ በዚህ አይነት መረጃዎቹ ከተሰበሰቡ በኋላ ሶስቱ የምልከታ ውጤቶች ተደምረው አማካይ ውጤታቸውን በመውሰድ ለትንተናው በጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

#### 3.2.1. ምልከታ

የክፍል ውስጥ ምልከታው በቪዲዮ ቀረጻ የታገዘ ነበር፡፡ የቪዲዮ ቀረጻው ተጠኝ መምህራን ሲያስተምሩ ለሁለት የትምህርት ክፍለ ጊዜ ያህል የተከናወነ ነው፡፡ ከተከናወኑት ሶስት የክፍል ውስጥ ምልከታዎች የመጀመሪያው ቀን ለማስመሰል ቀረጻ ተደርጎ ነጻ ምልከታ ተካሂዷል፡፡ የቪዲዮ ቀረጻው በአጋዥነት በምልከታ ያልታዩ ሁኔታዎችን እንደገና ለማጤን አስችሏል፡፡

#### 3.2.2.የጽሁፍ መጠይቅ

**የመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ**

ጥናቱን ለማካሄድም በጥቅም ላይ ከዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አንዱ ለመምህራን የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ ነው፡፡ ይህ የጽሑፍ መጠይቅ የተዘጋጀው የመስኩ ምሁራን (Geenalls and Swam(1986;3-4)፣ Alderson and Urqunent eds.(1984)Lunzer and Graner(1979፣42)) በተለያየ ጊዜ ካነሱዋቸው ትወራዎች በመውሰድ ስለ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች መረጃ ያስገኛሉ በተባለበት ሁኔታ ተደራጅተው ነው፡፡

**የተማሪዎች የጽሐፍ መጠይቅ**

የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ ከመምህራን የጽሐፍ መጠይቅ በተመሳሳይ መልኩ በአራት ክፍል የተከፈለ ነው፡፡ በውስጡም ክፍል አንድ የተማሪዎች አጠቃላይ መረጃ የሚጠይቁ ናቸው፡፡ በክፍል ሁለት አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት መረጃን የሚጠይቁ ዝግ ጥያቄዎች ናቸው፡፡

## 4.ትንታኔ

**በቅድመ ንባብ ደረጃ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የተሰጣቸው ትኩረት**

ተማሪዎች የንባብ ክሂል ማዳበር ይችሉ ዘንድ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች ትኩረት መሰጠት ተገቢ ነው፡፡በዚሁ መሰረት በቅድመ ንባብ ደረጃ መዳበር የሚገባቸው የመገመት ችሎታና ለቁልፍ ቃላት ፍቺ መስጠት ንዑሳን ክሂሎች ናቸው፡፡ የመገመት ችሎታ ያላቸው አንባቢዎች ርዕሱን በማየት በምንባቡ ሂደት ውስጥ ምን ሊመጣ እንደሚችል ቀድሞ ግምት ይሰጣሉ፡፡ በንባቡ ሂደትም ከግምታቸው ጋር ምን ያህል እንደተጣጣመ በመመዘን የመገንዘብ ደረጃቸውን ያጠናክራሉ፡፡ እንዲሁም ለቁልፍ ቃላት ፍቺ በመስጠት የምንባቡን ሀሳብ ለመረዳት ጥረት ያደርጋሉ፡፡ እነዚህ ንዑስ ክሂሎች በተመለከተ ተጠኚ መምህራኑ የሰጡት ትኩረት የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ሰንጠረዥ አንድ፣ **በቅድመ ንባብ ደረጃ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የተሰጣቸው ትኩረት ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ**

| ተ ቁ | ጥያቄ | ተከናውኗል | | አልተከናወነም | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ |
| 1 | በርዕሱ ዙሪያ ምን ምን ነጥብ ሊነሳ እንደሚችል እንዲገምቱ አድርገዋል፡፡ | 3 | 50% | 3 | 50 |
| 2 | ለቁልፍ ቃላት ፍቺ ሰጥተዋል፡፡ | 4 | 66.6% | 2 | 33.3 |

ሰንጠረዥ አንድ እንደተመለከተው በርዕሱ ዙሪያ ምን ሊነሳ እንደሚችል መገመትን በተመለከተ 3ቱ መምህራን ሲያከናውኑ 3ቱ መምህራን አላከናወኑም፡፡ ይህም የሚያሳየው ለንዑስ የንባብ ክሂሉ ግማሾቹ መምህራን ትኩረት መስጠታቸውን ነው፡፡ ይሁንና ግማሾቹ ሲያከናውኑ ባለመታየቱ በንዑስ ክሂሉ አተገባበር ረገድ ችግር እንዳለ ያሳያል ስለዚህ በርዕሱ ዙሪያ ምን ምን ነጥብ ሊነሳ እንደሚችል በመገመት ማስተማር ንዑስ ክሂል በተጠኚ መምህራኑ ትኩረት አግኝቷል ማለት ይቻላል፡፡

ለቁልፍ ቃላት ፍቺ የመስጠትንም ንዑስ የንባብ ክሂልን በተመለከተ በ4 መምህራን ተከናውኗል ፣ በ2 መምህራን አልተከናወነም፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለውን ንዑስ የንባብ ክሂሉ በአብዛኞቹ መምህራን ትኩረት የተሰጠው መሆኑን ነው ሆኖም 2 መምህራንም ቁጥር ቀላል የሚባል ስላልሆነ የንዑስ ክሂሉ አተገባበር

ፈጽሞ ከችግር የጸዳ ነው ለማለት አያስደፍርም። ይህንኑ በተመለከተ ለመምህራን በቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ በማነጻጸር ቀጥሎ ቀርቧል።

ሰንጠረዥ ሁለት፣ **በቅድመ ንባብ ደረጃ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የተሰጣቸው ትኩረት ከመምህራን መጠይቅ የተገኘ**

| ተራ ቁ. | ጥያቄ | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዘወትር እጠቀማለሁ | | አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ | | አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ | | ፈጽሞ አልጠቀምም | |
| | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ |
| 1 | የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ከሚማሩት ጋር በማያያዝ እንዲገምቱ ያደርጋሉ። | 3 | 50% | 3 | 50% | 0 | 0% | 0 | 0% |
| 2 | ለቁልፍ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ። | 4 | 66.6% | 1 | 16.7% | 1 | 16.7% | 0 | 0% |

በቅድመ ንባብ ደረጃ መዳበር ካለባቸው ንዑሳን የንባብ ክሂሎች አንዱ በቅድመ ንባብ የመገመት ችሎታ ነው። ይህን በተመለከተ ለመምህራኑ በቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ 3 (50%) መምህራን ዘወትር እጠቀማለሁ፣ ሲሉ 3(50%) መምህራን ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ ብለዋል።ከዚህ መረዳት የሚቻለው ተጠኝ መምህራን በከፍተኛ ደረጃ ለንዑስ ክሂሉ ትኩረት የሚሰጡ መሆኑን ነው። ይህ ደግሞ የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት መሠረት አድርጎ አዲስ ከሚማሩት ትምህርት ጋር በማያያዝ ማስተማር በከፍተኛ ደረጃ ለንዑስ ክሂሉ ትኩረት የሚሰጡ መሆኑን ነው። ይህ ደግሞ የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት መሠረት አድርጎ አዲስ ከሚማሩት ትምህርት ጋር በማያያዝ ማስተማር ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። በሌላም በኩል በተወሰነ ደረጃ ስለሚያቁት ነገር በስፋትና በጥልቀት እንዲመለከቱ ወይም ከሚያቁት ተነስተው ሌላ አዲስ ሀሳብ የመገንዘብ ችሎታ ለማዳበር ያስችላል። ይህንኑ ሁኔታ ተጠኝ መምህራኑ ትኩረት ሰጥተው ማስተማራቸው ጥሩ ጎን አለው።

ለቁልፍ ቃላት ፍቺ መስጠትንም በተመለከተ 4(66.6) ዘወትር እጠቀማለሁ፣1 (16.7%) መምህር አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ፤በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። በቅድመ ንባብ ደረጃ ለቁልፍ ቃላት ፍቺ መስጠት

ተማሪዎች ምንባቡን በሚያነቡበት ጊዜ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ቃላትን በማወቅ ሀሳቡን ለመረዳት የሚያስችላቸው በመሆኑ ይህንኑ ክሂል ተጠኝ መምህራኑ ትኩረት ሰጥተው ማስተማራቸው ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡

ከሰንጠረዥ ሶስት፣ **በቅድመ ንባብ ደረጃ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የተሰጣቸው ትኩረት ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ**

| ተራ ቁ. | ጥያቄ | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዘወትር እጠቀማለሁ | | አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ | | አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ | | ፈጽሞ አልጠቀምም | |
| | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ |
| 1 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ በርዕሱ ዙሪያ ምን ሊነገር እንደሚችል እንድትገምቱ ያደርጋሉ፡፡ | 61 | 46.3 % | 37 | 28% | 27 | 20.4% | 7 | 5.3% |
| 2 | ለቁልፍ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፡፡ | 84 | 66.6 % | 1 | 16.7 % | 1 | 16.7% | 0 | 0% |

ተጠኝ መምህራኑ በርዕሱ ዙሪያ ምን ሊነገር እንደሚችል ተማሪዎች እንዲገምቱ በማድረግ ስለማስተማራቸው 2 (46.3%) ተማሪዎች ዘወትር፣ 37(28%) ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ 27(20.3%) ተማሪዎች ጊዜ 7(5.3%)ተማሪዎች ፈጽሞ አይጠቀሙም፤ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በዚህ መረጃ አብዛኞቹ መምህራን ለንዑስ የንባብ ክሂሉ ትኩረት መስጠታቸውን ያመለክታል፡፡ ከተማሪዎች የተገኘው መረጃም ከክፍል ምልከታውም ሆነ ከመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ ተጠኝ መምህራኑ ለንዑስ የንባብ ክሂሉ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተዋል ማለት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል ተጠኝ መምህራኑ ለቁልፍ ቃላት ፍቺ እንደሚሰጡ ለማወቅ በቀረበው መጠይቅ 84(63.5%) ተማሪዎች ዘወትር፣31 (23.5%) ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ 15(11.4%) ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ 2(5) ተማሪዎች ደግሞ ፈጽሞ አይጠቀሙም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህም

አብዛኞቹ ተጠኝ መምህራን ለንዑስ ክሂሉ ከፍተኛ ትኩረት መስጠታቸውን ያመለክታል፡፡ ከፍተኛ ትኩረት መስጠታቸውም ንዑስ ክሂሉ በተገቢው ሁኔታ በተጠኚ መምህራኑ መተግበሩን ያሳያል፡፡

**በጊዜ ንባብ ደረጃ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የተሰጣቸው ትኩረት**

ሰንጠረዥ አራት፣ **በጊዜ ንባብ ደረጃ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎችን በተመለከተ ከክፍል ምልከታው የተገኘ**

| ተቁ. | ጥያቄ | ተከናውኗል | | አልተከናወነም | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ |
| 1 | ጥያቄዎችን በመስጠት የአሰሳ ንባብ እንዲያከናውኑ አድርገዋል፡፡ | 0 | 0% | 6 | 100% |
| 2 | መረጃዎችን ለይቶ ለማውጣት የገረፍታ ንባብ እንዲያከናውኑ አድርገዋል፡፡ | 0 | 0% | 6 | 100% |
| 3 | ስዕልን ማገናዘብ ወይም ቅጽ መሙላት ወይም ዝርዝር ጉዳዮችን በሰንጠረዥ መሙሉት መልመጃዎችን እንዲሰሩ አድርገዋል፡፡ | 0 | 0% | 6 | 100% |
| 4 | ንባብን በዝምታ ንባብ እንዲያነቡ አድርገዋል፡፡ | 0 | 0% | 6 | 100% |
| 5 | ከንባቡ ዝርዝር መረጃን እንዲያወጡ አድርገዋል፡፡ | 2 | 33.3% | 4 | 66.6% |
| 6 | ተማሪዎች የጽሁፉን አደረጃጀት መረዳታቸውን ጥያቄ በመጠየቅ አረጋግጠዋል፡፡ | 2 | 33.3% | 4 | 66.6% |
| 7 | የቃላትን ፍቺ ከአውድ አንጻር አንዲገምቱ አድርገዋል፡፡ | 6 | 100% | 0 | 0% |

በሰንጠረዥ አራት እንደተመለከተው ጥያቄዎች በመስጠት የአሰሳ ንባብ እንዲከናወን አድርገዋል በሚለው ረገድ በ6ቱም (100%) መምህራን አልተከናወነም፡፡ ይህም መረጃ የአሰሳ ንባብ በመምህራኑ ምንም ትኩረት እንዳልተሰጠው ያመለክታል፡፡

የአሰሳ ንባብ የተወሰኑ መረጃዎችን በምንባቡ ለማግኘት የሚደረግ ንባብ ሲሆን ይህን ችሎታ ለማዳበር መምህራኑ ያደረጉት ጥረት አለመኖሩ ደግሞ ተማሪዎች ተፈላጊ መረጃዎችን ለይቶ የማውጣት ችሎታ እንዳያዳብሩ ያደርጋቸዋል፡፡

መረጃዎችን ለይቶ ለማውጣት የገረፍታ ንባብ እንዲያከናውኑ ያደርጉ እንደሆነ ለማወቅ በተደረገው ምልከታ በ6ቱም (100%) መምህራን አልተከናወነም፡፡ ይህም የሚያመለክተው ተጠኚ መምህራኑ ለገረፍታ ንባብ ትኩረት የነፈጉ መሆናቸውን ነው፡፡የገረፍታ ንባብ የምንባቡን አጠቃላይ ሀሳብ ለማግኘት የሚደረግ የፍጥነት ንባብ ነው፡፡ በዚህ የንባብ ሂደትም የአንቀጽን ዐቢነገር ለይቶ ለማውጣት የምንባቡን ሀሳብ

ለማግኘት የሚካሄድ ንባብ ነው፡፡ ይህም አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ከፍ የሚያደርግ ነው፡፡ ይሁንና ተጠኚ መምህራኑ ይህን ጠቃሚ ክሂል ተግባራዊ ሲያደርጉ አልተስተዋለም፡፡

ሰንጠረዥ አምስት፣**በጊዜ ንባብ ደረጃ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የተሰጣቸው ትኩረት ከመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ**

| ተራ ቁ. | ጥያቄ | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዘወትር እጠቀማለሁ | | አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ | | አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ | | ፈጽሞ አልጠቀምም | |
| | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ |
| 1 | ጥያቄዎችን በመስጠት /ከ2-3 /የአሰሳ ወይም የገረፍታ ንባብ እንዲያከናውኑ ያደርጋሉ፡፡ | 0 | 0% | 1 | 16.7% | 4 | 66.6% | 1 | 16.7% |
| 2 | ስዕልን ማገናዘብ ወይም ቅጽን መሙላት ወይምዝርዝር ጉዳዮች በሰንጠረዥመሙላት የመሳሰሉ መልመጃዎችን ተማሪዎች እንዲሰሩ ያደርጋሉ፡፡ | 1 | 16.7% | 1 | 16.7% | 3 | 50% | 1 | 16.7% |
| 3 | ተማሪዎች ንባቡን በዝምታ ንባብ እንዲያነቡ ያደርጋሉ፡፡ | 0 | 0% | 1 | 16.7 % | 3 | 50% | 2 | 33.3% |
| 4 | ተማሪዎች ከንባቡን ዝርዝር መረጃን እንዲያወጡ ያደርጋሉ፡፡ | 0 | 0% | 3 | 50% | 2 | 33.3% | 1 | 16.7% |
| 5 | ተማሪዎች የጽሑፉን አደረጃጀት እንዲናገሩ ያደርጋሉ፡፡ | 2 | 33.3% | 2 | 33.3% | 2 | 33.3% | 0 | 0% |
| 6 | ተማሪዎች የቃላትን ፍቺ ከአውድ አንጻር እንዲገምቱ ያደርጋሉ፡፡ | 4 | 66. 6% | 1 | 16.7% | 1 | 16.7% | 0 | 0% |

ጥያቄዎች በመስጠት የአሰሳ ንባብ ያከናውኑ እንደሆነ ለተጠየቁት ጥያቄ 1 (16.7%) መምህር አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ፤4 (66.6%) መምህር አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ፤ 1 (16.7%) መምህር ፈጽሞ

አልጠቀምም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ አብዛኞቹ መምህራን አንዳንድ ጊዜ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ የሰጡት መረጃ በክፍል ምልከታ ከታየው ጋር የሚቃረን ሆኖ ነው የታየው፡፡ ፈጽሞ አለመጠቀማቸውን የገለጹት አንድ መምህር ብቻ ናቸው፡፡

ሌላው ንዑስ የንባብ ክሂል ስዕልን ማገናዘብ ወይንም ቅጽን መሙላት ወይንም ዝርዝር ጉዳዮችን በሰንጠረዥ መሙላት የመሳሰሉትን መልመጃዎች ያከናውኑ እንደሆነ ለተጠየቁት ጥያቄ 1 (16.7%) መምህር ዘወትር እጠቀማለሁ፤1 (1.67%) አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ፤3 (50%) መምህር አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ፤ 1(16.7%) መምህር ፈጽሞ አልጠቀምም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህም አብዛኞቹ መምህራን ንዑስ ክሂሉን አንዳንድ ጊዜ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ነው፡፡ይሁን እንጂ በክፍል ምልከታው እንደታየው አንድም መምህር ሲተገብረው አልታየም፤ ስለዚህ አብዛኞቹ ተጠኚ መምህራን ለንዑስ ክሂሉ ምንም የተሰጠው ትኩረት የለም ለማለት ያስደፍራል፡፡

ሰንጠረዥ ስድስት፤ **በጊዜ ንባብ ደረጃ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የተሰጣቸው ትኩረት ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ**

| ተራ ቁ. | ጥያቄ | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዘወትር ይጠቀማሉ | | አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማሉ | | አንዳንድ ጊዜ ይጠቀማሉ | | ፈጽሞ አይጠቀሙም | |
| | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ |
| 1 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ የንባብ አይነቶችን /የአሰሳ ግርፍ/ እንደአስፈላጊነታቸው እንድትጠቀሙ ያደርጋሉ፡፡ | 42 | 32% | 36 | 27% | 41 | 31% | 13 | 10% |
| 2 | ስዕልን ማገናዘብ ወይም ቅጽን መሙላት ወይም ዝርዝር ጉዳዮች በሰንጠረዥመሙላት የመሳሰሉ መልመጃዎችን እንድትሰሩ ያደርጋሉ፡፡ | 24 | 18% | 28 | 21% | 42 | 32% | 38 | 29% |
| 3 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ በዝምታ ንባብ እንድታከናውኑ ያደርጋማወጣትሉ፡፡ | 65 | 49% | 34 | 26% | 19 | 14% | 14 | 11% |
| 4 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ ከንባቡን ዝርዝር መረጃዎችን ለይቶ ማውጣት ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡ | 62 | 47% | 33 | 25% | 26 | 20% | 11 | 8% |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ የጽሑፉን አደረጃጀት እንድትናገሩ ያደርጋሉ። | 31 | 24% | 44 | 33% | 49 | 37% | 8 | 6% |
| 6 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ የቃላትን ፍቺ ከአውድ አንጻር እንድትገምቱ ያደርጋሉ። | 52 | 39% | 35 | 27% | 37 | 28% | 8 | 6% |

የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ የንባብ አይነቶችን /የአሰሳ ግርፍ/ እንደአስፈላጊነታቸው ስለመጠቀማቸው 42 (32%) ዘወትር ይጠቀማሉ 30 (27%) አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማሉ 41 (31 %)አንዳንድ ጊዜ ይጠቀማሉ 13 (10%) ፈጽሞ አይጠቀሙም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ የሚያመለክተው ስለንባብ አይነቶቹ በቂ ግንዛቤ እንደሌላቸው ነው።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ስዕልን ማገናዘብ ወይንም ቅጽ መሙላት ወይም ዝርዝር ጉዳዮችን በሠንጠረዥ መሙላት የመሳሰሉ መልመጃዎችን እንድትሰሩ ያደርጋሉ ተብለው ለተጠየቁት የጽሁፍ መጠይቅ 24 (18%) ተማሪዎች ዘወትር ይጠቀማሉ 30 (27%) አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማሉ 41 (31%) አንዳንድ ጊዜ ይጠቀማሉ 13 (10%)ፈጽሞ አይጠቀሙም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል።

**በድህረ ንባብ ደረጃ ለንውሳን የንባብ ክሂሎች የተሰጣቸው ትኩረት**

ሰንጠረዥ ሰባት፣ **በድህረ ንባብ ደረጃ ለንውሳን የንባብ ክሂሎች የተሰጣቸው ትኩረት ከክፍል ምልከታው የተገኘ መረጃ**

| ተቁ. | ጥያቄ | ተከናውኗል | | አልተከናወነም | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ |
| 1 | ተማሪዎች አጠቃላይ የምንባቡን ሀሳብ መረዳታቸውን መምህሩ ጥያቄ በመጠየቅ አረጋግጠዋል። | 6 | 100% | 0 | 0% |
| 2 | ተማሪዎች ምንባቡ እንዲገመግሙ አድርገዋል። | 2 | 33.3% | 4 | 66.6% |
| 3 | ከንባብ ጋር ሌሎችን ክሂሎች ጋር በማጣመር ጥያቄ አቅርበዋል። | 6 | 100% | 0 | 0% |

በምልከታው በ6ቱም (100%) መምህራን ተግባራዊ መደረጉን መረጃው ያሳያል። በመሆኑም አጠቃላይ የምንባቡን ሀሳብ መረዳት ንዑስ የንባብ ክሂል ከተጠኚ መምህራኑ ከፍተኛ ትኩረት እንደተሰጠው ያመለክታል።

በድህረ ንባብ ጊዜ ከሚከናወነው ተግባር አንዱ ተማሪዎች የምንባቡን አጠቃላይ ሀሳብ መረዳታቸውን ጥቃቄ በመጠየቅ ማረጋገጥ ነው፡፡ ይህንንም ተግባር ተጠኚ መምህራኑ በሙሉ ተግባራዊ ማድረጋቸውን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ሰንጠረዥ ስምንት፣ **በድህረ ንባብ ደረጃ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የተሰጣቸው ትኩረት ከመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ**

| ተራ ቁ. | ጥያቄ | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዘወትር እጠቀማለሁ | | አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ | | አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ | | ፈጽሞ አልጠቀምም | |
| | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ |
| 1 | ተማሪዎች አጠቃላይ የምንባቡን ሀሳብ መረዳታቸውን ጥያቄ በመጠየቅ አረጋግጠዋል፡፡ | 3 | 50% | 2 | 33.3% | 1 | 16.7% | 0 | 0% |
| 2 | ተማሪዎች ምንባቡን እንዲገመግሙ /ጥሩ መሆኑን መስማማታቸውን፣አለመስማማታቸውን/ያደርጋሉ፡፡ | 1 | 16.7% | 3 | 50% | 1 | 16.7% | 0 | 0% |
| 3 | የንባብን ትምህርት ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማቀናጀት ያቀርባሉ፡፡ | 3 | 50% | 2 | 33.3 % | 1 | 16.7% | 0 | 0% |

ተማሪዎች አጠቃላይ የምንባቡን ሀሳብ መረዳታቸውን ስለመጠየቃቸው ተጠኚ መምህራኑ በሰጡት ምላሽ 3 (50%) መምህራን ዘወትር እጠቀማለሁ 2 (33%) አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ 1 (16.7%) አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው አብዛኛዎቹ መምህራን ለዚህ ንዑስ ክሂል ትኩረት መስጠታቸውን ነው፡፡

**ሰንጠረዥ ዘጠኝ ፣ በድህረ ንባብ ደረጃ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የተሰጣቸው ትኩረት ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ**

| ተራ ቁ. | ጥያቄ | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዘወትር ይጠቀማሉ | | አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማሉ | | አንዳንድ ጊዜይጠቀማሉ | | ፈጽሞ አይጠቀሙም | |
| | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ |
| 1 | ከንባብ በኋላ አጠቃላይ የምንባቡን ሀሳብ መረዳታቸውን ለማረጋገጥ መምህራችሁ ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡ | 83 | 63% | 22 | 17% | 20 | 15% | 7 | 5% |
| 2 | ምንባቡን እንድትገመግሙ /ጥሩ መሆኑን መስማማታቸሁን፣አለመስማማታቸሁን/ ያደርጋሉ፡፡ | 36 | 27% | 35 | 27% | 37 | 28% | 24 | 18% |
| 3 | መምህራችሁ የንባብን ትምህርት ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማያያዝ ያቀርባሉ፡፡ | 62 | 47% | 34 | 26% | 23 | 17% | 13 | 10% |

የምንባቡን አጠቃላይ ሀሳብ መረዳታቸውን በመምህራቸው ስለመጠየቃቸው 83 (63%) ተማሪዎች ዘወትር ይጠቀማሉ 22 (17%) ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማሉ 20 (15%) ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ ይጠቀማሉ 7 (5%)ተማሪዎች ፈጽሞ አይጠቀሙም በማለት መልሰዋል፡፡ ከመረጃው እንደታየው አብዛኛዎቹ መምህራን አጠቃላይ ሀሳቡን መረዳት ንዑስ የንባብ ክሂል ትኩረት የሰጡ መሆኑን ነው፡፡ ይህም መረጃ ከክፍል ምልከታው እና ከመምህራን መጠይቅ ጋር ተቀራራቢነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## 5.ማጠቃለያና አስተያየት

### 5.1.ማጠቃለያ

ሀ) በቅድመ ንባብ ደረጃ መዳበር የሚገባቸው ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ተመሳሳይ የትኩረት ደረጃ እንደተሰጣቸው ተረጋግጧል፡፡ እነዚህም ንዑሳን የንባብ ክሂሎች የመገመት ችሎታና የቁልፍ ቃላትን ፍቺ ማወቅ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች በአብዛኛዎቹ ተጠኚ መምህራን ትኩረት የተሰጣቸው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ለ) በጊዜ ንባብ ደረጃ መምህሩ ከሚያከናውናቸው ተግባራት ውስጥ ጊዜ ወስኖ መስጠት በመምህራኑ ያልተከናወነ ሲሆን የንባብ ትምህርት ይቀርብ የነበረው በተማሪዎች ወይም በመምህራን በ□ ክታ ንባብ ነበር፡፡

ሐ) በጊዜ ንባብ ደረጃ መዳበር የሚገባቸው ንዑሳን የንባብ ክሂሎች በተለያየ ደረጃ ትኩረት የተሰጣቸው መሆኑን ተረጋግጧል፡፡ በዚህ መሠረት በጊዜ ንባብ ደረጃ መዳበር የሚገባቸው ንዑሳን የንባብ ክሂሎች መካከል የአሰሳ የገረፍታ የዝምታ ንባብ እንዲሁም ስዕልን ማገናዘብ ወይም ቅጽን መሙላት ወይም ዝርዝር ጉዳዮችን በሰንጠረዥ መሙላት ምንም ትኩረት እንዳልተሰጣቸው ጥናቱ አሳይቷል፡፡ አነስተኛ ትኩረት የተሰጣቸው ንዑሳን ክሂሎች ከንባብ ዝርዝር መረጃን ማውጣትና የጽሑፍን አደረጃጀት መረዳት ናቸው፡፡ ከፍተኛ ትኩረት ያገኘው ደግሞ የቃላትን ፍቺ ከአውድ አንጻር መገመት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

መ) በድህረ ንባብ ደረጃ የንባብ ትምህርት ሲሰጥ መምህሩ ከሚያከናውነው ተግባር አንዱ የቀረበውን ምንባብ ከተማሪዎች ገጠመኝ ጋር በማያያዝ እንዲገነዘቡ ማድረግ ነው፡፡ ይህም ሁኔታ በአብዛኞቹ ተጠኚ መምህራን ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን፣ በዚህ ደረጃ ንዑሳን ክሂሎችን በተመለከተ የተገኘው ውጤት የምንባቡን አጠቃላይ ሀሳብ መረዳት ንዑስ ክሂል እና የንባብን ትምህርት ከሌሎች ክሂሎች ጋር ማጣመር ንዑስ የንባብ ክሂል ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸው ሲሆን፣ የቀረበውን ምንባብ መገምገም ደግሞ አነስተኛ ትኩረት የተሰጠው መሆኑ ጥናቱ አመላክቷል፡፡

ተጠኚ መምህራኑ ስለንዑሳን የንባብ ክሂሎች ያላቸው ግንዛቤ ለማወቅ በክፍት ጥያቄና በቃለ መጠይቅ በተደረገው ፍተሻ በቂ ግንዛቤ የሌላቸው መሆኑን መረጃው ያሳያል፡፡

## 5.2.አስተያየት

ሀ) በቅድመ ንባብ ደረጃ ተማሪዎችን ማወያየትና በቡድን በማደራጀት እንዲወያዩ ማድረግ ትኩረት የተነፈገው በመሆኑ ለዚህ ንዑስ ክሂል አቻ ሁኔታን በመፈለግ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት ቢደረግ፣

ለ) በቅድመ ንባብ ደረጃ መዳበር የሚገባቸውን ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ማለትም የመገመት ችሎታና ለቁልፍ ቃላት ፍቺ መስጠት ተገቢ ትኩረት ያገኙ በመሆኑ ሌሎችም ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ተመሳሳይ የሆነ ትኩረት ቢያገኙ፣

ሐ) በጊዜ ንባብ ደረጃ ንዑሳን የንባብ ክሂሎችን መተግበር ላይ ትልቅ ድክመት የታየበት ደረጃ ነው፡፡ አብዛኞቹ መምህራን ተግባራዊ ያደረጓቸው ንዑሳን የንባብ ክሂሎችም በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በቀረቡት በቅድመ ንባብ የመወያያ ጥያቄዎችና ከድህረ ንባብ በኋላ በሚቀርቡ መልመጃዎች ትኩረት ለተሰጣቸው ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ነው፡፡ ከዚህም ከተጨማሪ ከራሳቸውም ሆነ ከመጽሔት የሚመርጧቸው ጽሑፎች ጥሩ ጎን ቢኖራቸውም በአላማው መሰረት የተመረጡ ቢሆኑ፣

መ) የአሰሳ ንባብ የገረፍታ ንባብ ስዕልን ማገናዘብ ወይም ቅጽን መሙላት ወይም ዝርዝር ጉዳዮችን በሠንጠረዥ መሙላት ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ምንም ትኩረት ያላገኙ በመሆኑ ትኩረት ቢሰጣቸው መልካም ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠኝ መምህራኑ ስለ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች በቂ ግንዛቤ የሌላቸው በመሆኑ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የትምህርትና ስልጠና ክፍሎች አጫጭር ስልጠናዎች ተዘጋጅተው የመምህራኑ ግንዛቤ የሚያዳብርበት ሁኔታ ቢመቻች፣

ሠ) በድህረ ንባብ ደረጃ ተማሪዎች የመገምገም ችሎታቸውን ለማዳበር የሚያግዛቸው ንዑስ የንባብ ክሂል ትኩረት አልተሰጠውም፡፡ በመሆኑም መምህራን ከመማሪያ መጽሐፍ ውጭ ከተለያዩ የጽሑፍ ምንጮች ምንባብ ሲመርጡ አነስተኛ ትኩረት የተሰጣቸውን ንዑስ የንባብ ክሂሎች ሊያለማምዱ የሚችሉ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት የታየውን ክፍተት ቢያሟሉ፣

ስለዚህ የንባብ ክሂል በተገቢው ሁኔታ ለማስተማር እንዲችሉ የማስተማሪያና የተማሪው መጽሐፍ ንዑሳን ክሂሎችን ለማዳበር በሚያስችል መልኩ ታስቦባቸው የሚዘጋጁ መሆኑ መልካም ነው፡፡ ለዚህም መነሻ ምክንያት የሆነው በዚህ ጥናት ውጤት እንደታየው ተጠኚ መምህራኑ ትኩረት ሰጥተው ተግባራዊ ያደረጓቸው በመማሪያ መጽሐፉ በቅድመ ንባብ የመወያያ ጥያቄዎችና በድህረ ንባብ መልመጃዎች ውስጥ ትኩረት የተሰጣቸውን ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ብቻ ነው፡፡

## ዋቢዎች

በድሉ ዋቅጅራ፡፡ (1996)፡፡ በስነ-ጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር ፡፡አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

አለም እሸቱ፡፡(1995)፡፡"በሁለተኛ ቋንቋ የማስተማሪያ መሠሪያ ዝግጅት ሂደት ውስጥ የክሂሎች አደረጃጀትና ትኩረት የሚሸሉ ይዘቶች አወቃቀር ከጥቅምት 25-29 ዓ.ም. ለአማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የተዘጋጁ የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍሎች መርሀ ትምህርቶችን ለማሻሻል ለተዘጋጀው አውደ ጥናት ከሥ/ት/ዝ/ጥ/ጥ/ም ኢንስቲትዩት፣(ያልታተመ)፡፡

---------------፡፡(1992)፡፡*መሠረታዊ የምርምርና የዘገባ አጻጻፍ*፡፡ አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

Aebersold, J. Ann & Mary, L.F (1997). From Reader to Reading Teacher. New York: Cambridge University Press.

Alderson, J and Urquhart, A. (Eds.). (1984). Reading in a Foreign Language. London: Longman.

Atkins, J. and et. al.(1996). Skill Development Methodology: Part 2. Addis Ababa: Addis Abeba University Press.

BBC, (2007). "British Council Teaching English-Reading Theories of Reading" Fromhttp://www.teaching English.org.uk/think/read/reading Theories.shtm/

Celec-murcia, M.(1991).Teaching English as a Second Language. Boston: Heinle and Heinle Publishers Davies, F. (1995).Introducing Reading .London: Penguin.

Cooper, M. and Fox, M.(1997). Junior English Reading. London: Longman.

Davies, F. (1995).Introducing Reading .London: Penguin.

Dreyer, L.G. (1984). "Readability and Responsibility" Journal of reading 27.4: 558-565

Dubin, F. and David, B.(1991). "Academic Reading and the ESL/EFL Teaching" In Celec-murcia,M.(Eds.).Teaching English as a Second Foreign Language. Boston: Heinleand Heinle Publishers.

Grellet, F.(1981).Developing Reading skill. London: Cambridge University Press

Harmer, J. (1991). The Practice of English Language Teaching. London: Longman.

Greenall, S.andSwan,M.(1986).Effective Reading: Reading Skills for Advanced Students. Cambridge: Cambridge University Press.

Harrison, C. (1980). Reading in the Classroom .New York: Cambridge University Press.

Hatch, E. and Farhady, H. (1982). Research Design and Statistics for Applied Linguistics. Newbury: House Publishers, Inc.

Haverson, W. (1991). "Adult Literacy Training" In Celec-murcia,M,(Eds.). English as a Second Foreign Language. Boston: Heinle and Heinle.

Heaton, J. B. (1991). Writing English Language Tests. New York: Longman

Hosenfeld, C. (1979). A Learner in Today's Foreign Language Classroom. Cambridge: Cambridge University Press.

Kaplam.R. (Edt.). (2000) The Oxford Book Of Applied Linguistic. Oxford: Oxford University Press.

Kothari,C.(2004). Research Methodology; Methods and Techniques.(2nd ed.) Delhi;NIC Publisher.

Muijs,D. (2004). Doing Quantitative Research in Education with SPSS. New Delhi: SAGE Publication Ltd.

Nuttal, C.(1982). Teaching Reading Skills for in a Foreign Language. London: Heinemann Educational and Professional Publishing Limited.

--------------. (2000). Teaching Reading Skills in Foreign Language. London: Heinemann Educational and Professional Publishing Limited.

Pupalia, A.(2000). "Interaction of Reader and Text" In Rivers, W. (1987).Interactive Language Teaching. New York: Cambridge: Cambridge University Press.

Rivers, W.(1987).Interactive Language Teaching New York Cambridge University Press.

Smith, F. (1978). Understanding Reading: A psycholinguistic analysis of reading and learning to read. New York: Holt, Rinehart and Winston.

---------------- (1985). Reading. Cambridge: Cambridge University Press.

Smith &Elley, F.(1997). How Children Learn to Read. London: Macmillan Ltd.

Wallace, C. (1992).Reading .Oxford: Oxford University Press.

William, E.(1984). Reading in the Classroom. London: Macmillan Publisher Ltd.

------------.(1993)."First and Second Language Reading Proficiency of Year 3, 4 & 6 Children in Malawi and Zambia." Journal of Reading in a foreign Language.V10 No 1.

Williams, E.(1983).Reading and Reading Comprehension .London. Macmillan. Ltd.